# ትግላችን




ልዩ ቁጥር

ነሀሴ 1961

# ትግላችን

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር

ወርሃዊ መፅሄት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

በአውሮፓ የኢ.ት.ተ.ማ. የ9ነኛው ጠቅላላ ጉባኤ ዜናዎች

አዘጋጅ፦— አንዳርጋቸው፡አሰግድ

1 Berlin 19

Harbigstr. 1

ነሀሴ 1691 ዋጋው፡ 1 ብር

ልዩ ቁጥር

1. ርእሰ-አንቀፅ 1
2. በሰሜን አሜሪካ የኢ.ት.ተ.ማህ.መልእክተኛ ያደረገው ንግግር 8
3. የማጋለጫ ትግል 20
– የዘጠነኛው ጠቅላላ ጉባኤ ኤግዚቢሽን 2[illegible]
– የሃያ ኪሎ ሜትር የተቃውሞ ጉዞ [illegible]3
– በማልመ ከተማ የተደረገው ንግግር 27
– ከተበተኑት ፅሁፎች አንደኛው 35
– የስዊድን አገር ጋዜጦች ትችት 38
– የእንግሊዝ አገር ቅርንጫፍ ማህበር የአንድነት ደብዳቤ 47
4. የአንድነት ደብዳቤዎችና ቴሌግራሞች 50
– ከልዩ ልዩ ድርጅቶች የተላኩ የአንድነት ደብዳቤዎ ች 62
5 የመንግስቱን ጋዜጦች ስናገላብጥ 62
6. ጊዜያዊ ዜናዎች 66
– የሁለተኛ ደረጃ ፈተናና ውጤቱ 66
– ከዩኒቨርስቲ ትምህርታቸውን ጨርሰው የወጡ ተማሪዎ
ች ስራ-ፈት ሆነዋል 67
– ታስረው የነበሩት ተፈቱ 68
– ጡረታ የገቡ ወታደሮች «አቤት» አሉ 69
7. ETHIOPIA፣ FEUDAL FASCISM 71

## መቅድም

ለአንድ ሬቮሉሽናዊ ድርጅት ከሚያስፈልጉት ዋና ዋና መሳሪያዎች አንዱ መፅሄት ነው።እርግጥ ነው፤አድሃሪዊ ድርጅቶም በመፅሄት ይጠቀማሉ።ነገር ግን የአድሃሪዊ መፅሄቶች ጥረት ድንቁርናን፣ፍርሃትን . . . በህዝብ መካከል ለመዝራት፣የበሰበሰንና ያለን ስርአት ዘለአለማዊ አስመስሎ ለማቅረብ ሲሆን የሬቮሉሽናዊያኖቹ ደግሞ እውቀትን፣ ድፍረትንና ራስን ማወቅን ለህዝብ ለማስተማር፣የበሰበሰ ስርአት መገልበጥ እንደሚገባው ለማሳየት ነው።

በመፅሄቶች ጠቃሚ ትምህርትን ለማስፋፋት፣መሰረታዊ አሳቦችን ለማሰራጨት እንደሚቻል በትክክል በመገንዘብ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ለየደረሱበት የተግል ደረጃ መሪ አሳብ ማሰራጫ የሚያገለግሉ መፅሄቶችን ማውጣት ከጀመሩ በርከት ያሉ አመታት አልፈዋል።

በመጀመሪያ በርከት ያሉ ቅርንጫፍ ማህበራት የየራሳቸው መፅሄቶች ነበሯቸው።የተማሪዎች ትግል ከፍ እያለ መሄድ የፖለቲካ ህሊናቸውን መዳበር ሲያስከትል የትግላቸውንም መቀናበር ጠየቀ። ለዚህ ነው በውስጥና በውጭ የሚገኙ ማህበሮቻችን በያሉበት ጠቅላይ ማህበሮቻቸውን ከፈጠሩ በኋላ የየራሳቸውን አዘጋጅ ቦርድ በማቋቋም በአውሮፓ ትግላችንንና ታጠቅን፣በሰሜን አሜሪካ "ቻሌንጅን" ፣በኢትዮጵያ ታገልን በተቀናበረ መልክ ማውጣት የጀመሩት።

አሁን ባለንበት ወቅት የተማሪዎች የትግል ደረጃ ከፍ ያለ ለመሆኑ በቤትም ሆነ በውጭ የሚያከናውኗቸው ሬቮሉሽናዊ ድርጊቶች ትክክለኛ ማስረጃዎች ናቸው።የደረሱበትን ከፍተኛ ፖለቲካዊ ህሊና ለመረዳት የቆሙባቸውንና የተሰለፉባቸውን አላማዎች መመልከት ብቻ ይበቃል።አሁን መከተል የነበረበት እርምጃ ትግሉን በበለጠ ማቀናበር ነበር።

በዚህ ታሪካዊ ፍላጎት ተፀንሶ የተወለደው አለም-አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ከተቆረቆረበት ጊዜ አንስቶ እንደዋና ተግባር አርጎ የወሰደው የስራ ፕሮግራም በያለበት የሚካሄደውን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ትግል ማቀናበር ነው።የአለም አቀፉ ጊዜያዊ ስራ አስኪያጅ ኮሚቴ ባደረጋቸው ሁለት ስብሰባዎች ላይ ዝርዝር የስራ ፕሮግራም እያወጣ ለአባል ማህበራት አስተላልፎአል፤ስራቸውን ሊያከናውኑ የሚችሉበትን ዘዴ አንድ ባንድ ጠቅሶ አመልክቶአል።በዚህ አመት ሊየገር ውስጥ ከ"አፕሪል" 7 – 10.69 ባደረገው ስብሰባ ላይ ከተነጋገረባቸው ጉዳዮች አንዱ "የመፅሄት ማቀናበር" ዘዴ ነበር።

ከፍ ብለን እንደተናገርነው ሁሉ በየአገሩ(ኢትዮጵያ፣አሜሪካ፣ አውሮፓ )የሚገኙት አባል ማህበራት የየራሳቸው መፅሄቶች አሏቸው።አሁን የተደረሰበት የትግል ደረጃ ግን መፅሄቶቻችን በይዞታቸውም ሆነ ባስተታተማቸው በበለጠ ዘዴ እንዲቀናበሩ ይጠይቃል።ይህንን በመረዳት፣ ላይ በተጠቀሱት ቀናት በሊየገር የተሰበሰበው የአለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተሚሪዎች ማህበር ጊዜያዊ ኮሚቴ፣በጉዳዩ በሰፊው ሀሳብ ለሀሳብ ከተለዋወጠ በኋላ፣ከዚህ አመት ጀምሮ መፅሄቶቻችን በአለም አቀፍ ማህበር አቀናባሪነት እንዲዘጋጁ ወሰነ።መፅሄቶቻችንም‹አለም አቀፍ የኢዮጵያ ተማሪዎች ማህበር መፅሄት› በሚል ስም እንዲታወቁ ውሳኔ አሳለፈ።ውሳኔውን አባል ማህበራት በሙሉ ተቀብለውታል።

በፈረንሳይ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ቅርንጫፍ ማህበር ተዘጋጅቶ ለዘጠነኛው ጠቅላላ ጉባኤ የቀረበ ሬቮሉሽናዊ መዝሙር።

መሬት ላራሹ

መሬት ላራሹ
ለላብ አፍሳሹ
አገሩ ለላብ አደሩ
አገሩ ለሰራተኛው፣ለገበሬው ለባላገሩ

ተነስ ገበሬ ተንቀሀል
ከሞፈር ቀንበር ተቆጥረሀል
ለነፃነትህ ዋስትና ከትግልህ ሌላ የለምና

መሬት ላራሹ

ተነስ ሃይል ያንተ ነው በርታ
አንት ያሰርከውን ማን ሊፈታ
ተከፋፍለህ አትገዛ
ተነስ በአንድነት ጥቃት በዛ

መሬት ላራሹ

ተነስ ጣላቸው ሰርተው ይብሉ
አንት ባፈራኸው አያይሉ
በል አውርዳቸው እስቲ ይስሩ
እስከ መቼ ባንተ እሽሩሩ

መሬት ላራሹ

ተነስ ባላገር ንገራቸው
አገሩ የኔ ነው በላቸው
ሃያል መሆንህን አትርሳ
ድሉ ያንተ ነው ተነሳ

መሬት ላራሹ ...

## ርእሰ-አንቀፅ

## በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ዘጠነኛ ጠቅላላ ጉባኤ

ብዙ መሰናክሎችን አልፎ፣በአውሮፓ የኢ.ት.ተ.ማህ. 9ኛ ጠቅላላ ጉባኤ ከነሀሴ 2–11,1961 አ.ም. በደቡብ ስዊድን፣ሉንድ ከተባለችው ከተማ ውስጥ አመታዊ ስብሰባውን አድርጎ፣ ያቀደውን ስራ ከፈፀመ በኋላ ተለያይቷል።

የማህበሩ አባላት በጉባኤው ለመሳተፍ ከብዙ የአውሮፓ ከተሞች ረጅም ጉዞ አድርገው በእለቱና በስፍራው ተገኝተው ነበር።በስብሰባው ወቅት የጉባኤው ተሳታፊዎች በሙሉ ልብ ሲካፈሉ ቆይተዋል። በመጨረሻውም ጠቅላላ ስብሰባ ላይ መሰረታዊ በሆኑ ነገሮች ላይ ይደረጉ የነበሩት ክርክሮችና ትችቶች የኢትዮጵያ ተማሪዎች የኢትዮጵያንና የአለም-አቀፍ ፕሮብሌሞችን በትክክለኛ መንገድ መመርመርና መመልበት መጀመራቸውን በጉልህ ይመሰክሩ ነበር።

የ9ነኛው ጠቅላላ ጉባኤ ከቀድሞዎቹ ጠቅላላ ጉባኤዎች ባንዳንድ ነገሮች ይለያል።ከሚለይባቸውም ነገሮች አንደኛው የዘንድሮው ጉባኤ አመራርና ይዘት ቀደም ብሎ የተነደፈው በአለም-አቀፍ የኢ.ት.ማህ. ሲሆን፣ ሁለተኛው በአለም-አቀፉ ማህበር ውሳኔ መሰረት ጉባኤው በሴሚናር መልክ እንዲካሄድና ሴሚናሩም የሚነጋገርባቸው አርእስቶች ቀደም ብለው በቅርንጫፍ ማህበራት እንዲጠኑ መደረጉ ነው።

በአውሮፓ የኢ.ት.ተ.ማህ. በእንደዚህ አይነት መቀናበሩና መካሄዱ ትግላችን የደረሰበትን ደረጃ የሚያሳይ አይነተኛ መረጃ ነው። ይኸውም የትግል ደረጃ የሚያሳየን ( ሀገራችን ያሉት ቅራኔዎች እየከረሩ በሄዱ መጠንና የአድህሪው መን ገስት ጭቆና እየጨመረ በሄደ መጠን፣ተቃዋሚ ሀይሎች አንድ መልክ ባለው ድርጅታዊ ጥላ ስር ተከማችተው ትግላቸውን እያቀናበሩ ለመ የጋት መሰለፋቸውን ነው።

በተጨማሪ፣ 9ነኛውን ጠ ቅላላ ጉባኤ አይነተኛ የሚያደርገው፣የኢትዮጵያ ህዝብ ትግል የደረሰ ነት ታሪካዊ ደረጃ ነው። ይህ ታሪካዊ ደረጃ ምንድነው ? ዛሬ በሀገራ ችን ተጨቋኙ ህዝብ (ሰራተኛው፣ገበሬው፣ተማሪው፣ምሁራኑ... ) ያለው እርአት ያስፈርበትን ጭቆና ፈንቅ

ሎ ለመጣል በቁጣ የተነሳበት ታሪካዊ ወቅት ነው።እኛ ተማሪዎች የዚ
ህ ትግል አካል በመሆን ከተጨቆነውና ከተበዘበዘው ህዝብ ጋር ተዋህ
ደን በመታገል ነፃ ኢትዮጵያ እንድትመሰረት በላባችንና በደማችን እ
ንታገላለን በሚል ከፍተኛ አላማ ስር የተሰለፍንበት ጊዜ ነው። በሀገር
ቤትና በውጭ የሚገኙ ተማሪዎች ይህንኑ አላማ በተግባር ይመሰክራሉ፤
እየመሰከሩ ናቸው።

እንደዚህ ያለውን ትግል ለመምራት ከተጨባጭ ሁኔታ ው
ስጥ የፈለቀ ትክክለኛ ሳይንሳዊ እውቀት (ቴኦሪ) ይጠይቃል።አለም-አ
ቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ይህንን አስቀድሞ በመረዳት፣9ነኛ
ው ጠቅላላ ጉባኤ እንዲያጠናቸው ወስኗቸው የነበሩት አርእስቶች፣ የ
ሀገራችንን ሁኔታ አበጥሮ ለመረዳት እጅግ የሚረዱ ነበሩ።

«ኢኮኖሚ» በሚለው የጥናት አርእስት ስር ቀርቦ የነበረው
መሰረታዊ አሳብ፤ ከሁሉ በፊት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ሁኔታና የወደፊ
ት እድገት ከሌላው አለም – በተለይም ከተበዘበጋሮ አገሮች የእድገት
ታሪክ– ተነጥሎ ሊታይ እንደማይችል አስረድቷል።ከዚህም በላይ የኢ
ትዮጵያ ኢኮኖሚ በመሰረቱ ፊውዳል ሲሆን፤ የኢምፔሪያሊስቶች ወደ
አገራችን መግባት እንደምን እያጣመመውና እያወላገደው እንደሄደ
አሳይቷል።በንግድና በእንዱስትሪ በኩል፤ የአገሪቱ ንግድና እንዱስትሪ
በውጭ ሰዎችና በባእድ መንግስታት እጅ መያዛቸውን ከማር.ጋገጡም
በላይ፤የሀገራችን ባለገንዘቦች አጅግ ደካማ የሆኑ፤የውጭ ካፒታል ጥገ
ኞችና አገልጋዮች እንጂ፤በራሳቸው እግር ለመቆም የማይችሉ መሆና
ቸውን በማስረጃ አብራርቷል።በመጨረሻም ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እድ
ገት ዋና እንቅፋትና ጠላት የሆኑት የፊውዳሉ ስርአትና ኢምፔሪያሊዝ
ም መሆናቸውን ከጥናቱ በገኘው ውጤት አሳየ።

«የሰራተኛ፤የገበሬና የተማሪ ትግል» በሚለው አርእስት ስ
ር የቀረበው ጥናት፤የኢትዮጵያ ህዝብ ከፍ ያለ የትግል ታሪክ እንዳለው
በሰፊው ይተች ነበር።በዚህ አርእስት ስር እስታሁን የተደረገው ጥናት
እጅግ ጥቂት በመሆኑ፤ እያንዳንዳችን ያለፉትን የኢትዮጵያ ህዝብ ትግ
ሎች ተንትነን ባለማወቃችን ትክክለኛ ቦታቸውን አልሰጠናቸውም ነበ
ር።ጥናቱ፤ በሰፊው ከመዘገባቸው ትግሎች በላይ፤ የኢትዮጵያ ህዝብ እ



ስካሁንም የተጐናፀፋችውን ድሎች ያገኘው በታላቅ መስዋእትነት መ
ሆኑን አሳይቷል።ጊዜያዊውን የትግል ሁኔታ ቀረብ ብሎ በመመልከት
አሁን የኢትዮጵያ ሰራተኞች፤ገበሬዎችና ተማሪዎች የሚያደርጓቸው ት
ግሎች ከፍተኛ መሆናቸውን እያመለከተ፤ እነዚህ ህዝባዊ ትግሎች ወ
ደፊት ገስጋሽ በሆነ ሬቮሉሽናዊ ድርጅት ስር መቀናበርና መመራት እ
ንዳለባቸው የትግሉ ደረጃ የሚጠይቀው ዋናው ተግባር እንደሆነ አሳይ
ቷል።

‹ተግባራችን› በሚለው ጥናት ስር የቀረቡት ሀተታዎች አ
ዲሲቱን ኢትዮጵያ ለመመስረት፤ከሁሉ በፊት ከሰራተኛውና ከገበሬው
ጋር መዋሀድ ቀዳማዊ አላማችን መሆኑን እያሳሰበ፤ ለዚህ ሬቮሉሽናዊ
ተግባር ድርጅታችንን በበለጠ ማጠንከርና እውቀታችንንም ለማስፋት
ታላቅ ትግል ማድረግ እንደሚያስፈልገን አስገንዝቦናል።በተጨማሪ ደ
ግሞ ቀላል ድልን በመመኘት ለረጅምና ለመራራ ትግል ሳንዘጋጅ በቸ
ልተኝነት ከጠላቶቻችን ወጥመድ ውስጥ እንዳንገባ በጥንቃቄና በንቃት
መራመድ እንዳለብን በሰፊው አስረድቶናል።

በ9ነኛው ጉባኤ ላይ ብዙ የከረሩ አድሀሪ አስተያየቶች አ
ልተሰነዘሩም ነበር።ምናልባት ሁሉም ሙሉ በሙሉ በያንዳንዶቹ ጥያቄ
ዎች ላይ ስላልተናገሩ አድሀሪ አስተያየቶች ተዳፍነው ይሆናል። ከተጣ
ሉት አስተያየቶች ውስጥ አንዳንዶቹን ብንወስድ፤አልፎ አልፎ የትንሹ
ዋ-ቡርዡዋ አስተያየቶች መሰንዘራቸው አልቀረም።ለምሳሌ፡«የወታደር
ሀይል በስልጣን ላይ ያሉትን ወንበዴዎች ቢገፈትራቸው ነገሩ ያልቃል!
ለኢትዮጵያ ህዝብ በሩ ይከፈታል¡» የሚል ሀሳብ ነበር።ጉዳዩን እንመ
ልከተው።

የኢትዮጵያ ህዝብ በጭቆና ቀንበር ስር መውደቁን ይቀበላ
ሉ።ከዚያም ቀጥለው፤የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ወደኋላ የቀረ መሆኑን ያለ
ክርክር ያምኑበታል።ግን የሚዘነጉት አንድ አይነተኛ (የፕሪንስፕል) ጥ
ያቄ አለ።ይኸውም ለኢትዮጵይ ህዝብ መጨቆን፤ለኢትዮጵያ ህዝብ መ
በዝበዝና መዘረፍ፤ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ወደኋላ መቅረት ምንጭ የሆነው
የፊውዳሉ ስርአት መሆኑን ነው።በኢኮኖሚ አነጋገር ሲተረጐም ይህ የ
ሚያመለክተው፤ በአንድ በኩል በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት የእርባታ መ

ሳሪያዎች(ማለት፡መሬቱና እንዲሁም አልፎ አልፎ ብልጭ ያሉት ዘመ
ናዊ የእርባታ መሳሪያዎች .....) በጣት በሚቆጠሩ ሰዎች መያዛቸውንና
የዘጠና በመቶው ህዝብ የስራ-ፍሬ በእነሱ እጅ መግባቱን ሲሆን፡በሌላ
በኩል ደግም፡የእርባታ ሀይሎች ደረጃ ወደኋላ የቀረ መሆኑን ነው። እ
ኛ የምንለው ለውጥ እነዚህ የእርባታ መሳሪያዎች በህዝቡ እጅ ገብተ
ው ወደፊት ገስግሽ የሆነ የእርባታ ሀይል ሊወለድና ሊፋፋ የሚችልበ
ት ስርአት ይፈጠር ነው። «የወታደር አገዛዝ»መመኘት እኮ፡በአገራችን
ላሉት የእርባታ መሳሪያ ባለቤቶች አዲስ ጋሻ ጃግሬ እንመልምል ማለ
ት ነው።መሰረታዊው ጥያቄ ይህ ነው፤ለህዝብ ወይንስ ለአዲስ ጋሻ ጃግ
ሬ?

«የወታደር አገዛዝ» ወይም «ኩ-ዴታ» የሚያስከትለው ይ
ህ ከሆነ(ማለት፡እናቱ ላይ ያሉታን ገገሮች ብቻ መቀየር)፡«የወታደር
አጋዛዝን» የሚመኙ ሰዎች፡ምንም ያክል አገር-ወዳድ፡ምንም ያክል መ
ሰረታዊ ለውጥን ፈላጊ ቢሆኑ፡መሰረታዊውን ጥይቄ እስታልተረዱ ድረ
ስ የጥቂቶች መሳሪያ መሆናቸው አይቀርም።አንዳንዶቹ«የወታደር አገዛዝ
ን»የሚመኙት በኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ ላይ ለመውጣት መሰላል የሚ
ፈልጉ ግለሰባዊያን በመሆናቸው ነው። ለምን ይሄን እንላለን?

ደጋግመን ደጋግመን ስለኢምፔሪያሊዝም የምናወሳው ቃ
ሉን ስለወደድነው ሳይሆን፡በሀገራችን ውስጥ በሰፊው በመግባቱና የእ
ድገታችን ፀር መሆኑን በትክክል በመመልከታችን ነው። ኢምፔሪያሊ
ዝም —በተለይም የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም— የወታደር መንግስት
ሊያቋቁምልን እንደሚፈልግ የታሪክ ትምህርታችንና የየእለቱ ዜና (የ
ደቡብ አሜሪካ አገሮች፡ደቡብ ቪየትናም፡ደቡብ ኮሪያ፡ግሪክ፡ጋናና የተቀ
ሩት የአፍሪካ አገሮች ...) በግልፅ የሚያሳየን ነገር ነው።የኢትዮጵያ የ
ጦር ሀይል የሚመራው፤የሚሾመው፤ኮሪያና ኮንጎ የሚላከው፡የሚጫነ
ው፤ የሚታጠቀው፤የሚለብሰው የአሜሪካንን ኢምፔሪያሊዝም ፍላጎ
ት ለመጠበቅ ብቻ እኮ ነው።

አንዳንዴ ጠላቶቻችንን ብልጦች ሆነው እናገኛቸዋለን።በ
አገራችን የጦር ሀይል ውስጥ የሚፈፅሙትን ተግባር ግን በገሀድ የሚ
ያደርጉት ስለሆነ፡ይኸንን ካልተገነዘብን እኛ አልነቃንም ማለት ነው። እ



ነሱ ግን በየትም አገር የሚያደርጉት ነገር ነው። ኢምፔሪያሊዝም በኢ
ትዮጵያ ውስጥ የሚወስደው እርምጃ ከጥቅሙ ጋር የተያያዘ ነው። ዛሬ
አብሯቸው የሚዶልተው የፊውዳሉ መሪዎች ከጥቅሙ ጋር የሚጋጩ
ሲሆኑ፡እንደአለቀ ሸሚዝ አውልቆ ይጥላቸዋል።«የወታደር አገዛዝ» የ
ምንለው፡ኢምፔሪያሊዝም ሊያጠልቀው የፈለገውን አዲስ ሸሚዝ ነው።

የአገራችንን ሁኔታ አተኩረን ከተመለከትነው፡የሚመጣው
«ኩ-ዴታ» ባሜሪካኖች የታለመና የተደገፈ ብቻ ነው፤ ሊሆን የሚችለ
ው።ይህም ማለት፡ራሱ «የወታደር አገዛዝ» ወደኋላ ጉታች ከመሆኑም
በላይ፡በተጨማሪ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በአገራችን ላይ ለጣለው
የብዝበዛ ድንኳን ከሁሉ የበለጠ የጠነከረ ችካል ይሆነዋል ማለት ነው።
ሁኔታው ይህ ሆኖ ሳለ፡«የወታደርን አገዛዝ» የሚመኙ ግለሰባዊያን፡በ
መሰረቱ የሚመኙት የግል ጥቅማቸው የሚዳብርበትን «ለውጥ» ነው።
እነዚህ፤ ኢምፔሪያሊዝም በሚያርከፈክፍላቸው ጉርሻ ለመጠርቃት የ
ሚመኙ ግለሰባዊያን ለሰፊው ህዝብ ፍላጎትና ትግል ፀር መሆናቸው
ከቶ አያጠራጥርም።

አሁን በአገራችን ባለው የጦር ሀይል ላይ መውጪያችንን
መመልከት የኢትዮጵያ ህዝብ የሚዋጋበትን መሰረታዊ ሀሳብና የኢት
ዮጵያን ህዝብ እውነተኛ ጠላቶች ጠንቅቆ አለመገንዘብ ነው።የኢትዮጵ
ያ ህዝብ ጠላቶች ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም—በተለይም የአሜሪ
ካን ኢምፔሪያሊዝም— ናቸው፤ የሚታገለውም እነዚህን ጠላቶቹን አ
ጥፍቶ፡ራሱን በራሱ ሊያስተዳድር የሚችልበት ስርአት እንዲመጣ ነው
ይህ «በኩ-ዴታ» ሊመጣ አይችልም፤በሰፊውህዝብ ትግል እንጂ።

አንዳንዶቹ በወታደር ቃክ የሚመጣውን ኢምፔሪያሊዝም
በደንብ ይረዱት ይሆናል፤ ከዚህም የተነሳ ኢምፔሪያሊዝምን የመቋቋ
ም ሀሳብ ሊኖራቸው ይችላል። ነገር ግን እንደኮረት የተቀለለውን የኢ
ምፔሪያሊዝምን ሀይል ሲመለከቱ፡የፍርሀት ውሽንፍር ይገርፋቸውና ት
ግሉ ሜዳ ከመድረሳቸው በፊት አሞታቸው ይፈሳል፤ይሸነፋሉ።በዚህ አ
ኳሀን ውስጥ የሚገኙ ሰዎች በመሰረቱ ያልተገነዘቡት የህዝባዊን ሀይል
ታላቅነትና ከፍተኛነት ነው።ታሪክ የሚያሳየን የኢምፔሪያሊዚምን ሆነ
የፊውዳልዚምን ወይንም የማንኛቸውንም አድሀሪ ሀይል ሊቋቋመው የ

ሚችለው የሰፊው ህዝብ ሀይል (አልጄሪያ፣ጊኒ ቢሳው፣ቪየትናም ... ኢ ትዮጵያ በጠላት ወረራ ዘመን) መሆኑን ብቻ ነው።እርግጥ! ትግሉ ጊዜ ይወስዳል፣መስዋእትነትንም ይጠይቃል። ግን ለኢትዮጵያ ህዝብ ድልን ሊያጐናፅፈው የሚችለው የዚህ አይነቱ ትግል ብቻ ነው።

ይህ የሚያሳስበን በአባላት መካከል ከፍ ባለ ደረጃ የሪቮሉሽናዊ እውቀት እንዲሰራጭ ያለእረፍት መጣር እንዳለብን ነው። ያለበለዚያ በቅንነት የተነሱ ጓዶች ጭምር፣ ከባድ መስሎ ለሚታያቸው ፕሮብሌም አቋራጭ መንገድ ሲፈልጉ፣ ጠላቶቻችን ወጥመድ ውስጥ በመግባት በረጅሙ ላሰብነው ትግል አነስተኛ እንቅፋት ሊሆኑ ይችላሉ።ይህ እንዳይሆን ሌት ተቀን መጣር አለብን።

በእውቀትና(ቴኦሪ) በድርጊት መካከል ያለውን ግኑኝነት ያልተረዱ ይህ የ 9ነኛው ጠቅላላ ጉባኤ ለምን እንደተደረገ ጉልቶ ላይታያቸው ይችላል።ነገር ግን ማናቸውንም የኢትዮጵያ ጉዳዮች ሊጨበጡ በሚችሉ ማስረጃዎች ላይ ተመርኩዞ በመመርመር፣በታቸውን አፍታቶ ለማወቅና ውስጣዊ ግኑኝነታቸውን አረጋግጦ የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃ የሚወጣበትን መንገድ በዚህ እውቀት ላይ ለመመስረት ነው። አንዳንዶቹ የቴኦሪን እውቀት ዝቅ ለማድረግ ይሞክራሉ፤ ሌሎቹ ደግሞ የቴኦሪ እውቀትን እንደመጨረሻ አድርገው በመውሰድ የአእምሮ ማንቀሳቀሻ ብቻ ያደርጉታል።ከመጀመሪያዎቹ ውስጥ ድርጅታዊ ትግልን የሚያራክሱ፣«የወታደር አገዛዝ» ተመኚዎች ሁሉ ይገቡበታል። ከሁለተኛው ውስጥ ደግሞ ግለሰባዊያን የሆኑ፣ ከስርአቱ ለመጠቀም የሚፈልጉ፣የምእራባዊይን ርእዮተ-አለም የነደፋቸው በሙላ ይገባሉ።

ምናልባት የዘንድሮው አመራር የተለየ በመሆኑ፣የቀረቡት ጥናቶች በሙብዛታቸው፣ እንዲሁም ጠለቅ ያሉ ፕሮብሌሞችን በመመርመራቸው ሁላችንም እንደፈለግነው ያህል ለመሳተፍ ጊዜ አልነበረንም። ጥቂቶቻችን ደግሞ ከጥናቶቹ ጋር ትይዩ በሆነ ደረጃ የርእዮተ-አለማችንን አላራመድንም ነበር።

9ነኛው ጠቅላላ ጉባኤ ለአገራችን ፕሮብሌሞች መፍትሂ ለማግኘት መጀመሪያ ችግሮቹን አጣርተን ከማወቅ መነሳት እንዳለብን ያስረዳናል።በዚህም ረገድ በረጅሙ ለታቀደው‹የማወቅ ዘመቻ እንቅስቃ



ሴ›እንደበር ከፋች ሊቆጠር ይገባዋል።በየቦታው የተቋቋሙት «የህዝባዊት ኢትዮጵያ ኮሚቴዎች» «በማወቅ ዘመቻ» ትግል ውስጥ ተቀዳሚ ቦታ ሊኖራቸው ይገባል። እስካሁን ከሰሩት በላይ ወደፊት በይበልጥ መስራትና መታገል አለባቸው።

በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር መልእክተኛ በ9ነኛው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ መገኘትና በዚያ የሚገኙ ጓዶች ያደረጉትን ትግል መግለፅ ለጉባኤው አስተሳሰብ በጣም ረድቷል።የኢትዮጵያ ተማሪዎች በአንድነት መታገል፣ የወደፊት ተራማጅ ድርጅቶችን ድጋፍ በመፈለግ ከታጋዩ የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር እንዲሰለፉ መጣር ከዋናዎቹ ተግባሮቻችን አንዱ ነው ።

9ነኛው ጠቅላላ ጉባኤ በስራው መደምደሚያ ላይ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ያለእረፍት የሚፈፀመውን ጭቆና በመቃወም፣የህዝባችንን ጠላቶች –ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም– በመቃወም፣ አድሀሪውን መንግስት በማጋለጥ፣ የህዝቡን ትግል በ መደገፍ የሃያ ኪሎ ሜትር (ከሉንድ እስከ ማልመ የተባለው ከተማ ድረስ) የተቃውሞ ሰልፍ አድርጐ፣ከኢትዮጵያ ሰራተኛ ጐን መሆኑን አረጋግጦአል። ይኼ በድርጅታችን ታሪክ ከፍ ያለ ስፍራ ሊሰጠው ይገባል ።

የአለም-አቀፍ ማህበራችን በ9ነኛው ጠቅላላ ጉባኤያችን የተጀመረው ‹የማወቅ ዘመቻ እንቅስቃሴ» በየአመቱ መጨረሻ ላይ በመገናኘት የሚፈፀም ሳይሆን፣በየአካባቢው የሚገኙ አባላት በየጊዜው እየተገናኙ እንዲወያዩ፣ጥናቶች እንዲሰራጩ፣ከተግባር ጋር እንዲያያዙና እንዲተሰሰሩ መምሪያ መስጠት ይኖርበታል።«የማወቅ ዘመቻ እንቅስቃሴ»በፕሮግራማችን ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ከሚሰጣቸው ጉዳዮች አንደኛው ነው።

ትግላችን በጥልቀቱም በስፋቱም
እያደገ በመሄድ ላይ ነው!
ቆርጠን በመነሳት ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ እንታገል!
የኢትዮጵያ ህዝብ ያሸንፋል!

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት፤በአለም አቀፉ ማህበራቸ
ው መሪነት፤አሳብ መለዋወጥን፤የስራ ፕሮግራማቸውን ማቀናበርንና ተግ
ባር መከፋፈልን ከጀመሩ ጥቂት አመታት አልፈዋል።በዚሁ መሰረት ከ
ሰሜን አሜሪካ የኢ.ት.ተ.ማ. አንድ መልእክተኛ፤ጓድ እንድርያስ እሸቴ፤
በአ.የኢ.ት.ተ.ማ. ፱ነኛ ጉባኤ ላይ ተገኝቶ ስለማህበራቸው ሁኔታና ስለት
ግላቸው ዘዴ በሰፊው አስረድቶናል።

ከኢ.ት.ዩኒቨርሲቲ ተ. ማህበርም መልእክተኛ እንዲመጣ ተ
ሞክሮ ነበር።ግን ፋሽስታዊው አገዛዝ የመውጫ በሩን ሁሉ ስለዘጋው
ይህ አሳብ ለጊዜው ከስራ ላይ ሊውል አልቻለም።

ትግላችን እያደገ በሄደ ቁጥር ህብረታችን ይዳብራል።የሚዳ
ብረው ህብረታችን በተራው ትግላችንን ከፍ ያደርገዋል።ህብረታችን ይ
ጠንክር!

---

<u>የጓድ እንድርስ ንግግር</u>

ውድ ጓዶች፤እህቶችና ወንድሞች

አስቀድሜ ከሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበ
ር የጓድነት ሰላምታችንን አቀርብላችኋለሁ፤ውይይታችሁ መልካም ው
ጤት ይኖረው ዘንድ ያለን ምኞት ከፍተኛ ነው።የአድህሪው መንግስት
መሪ ሀይለ ስላሴ ኢትዮጵያን ለሀራጅ ሽያጭ ለማቅረብ (እስከሁን የሸ
ጠው አንሶት) በሰሜን አሜሪካ በቅርቡ በተገኘበት ወቅት ስላደረግነው
ትግልና በጠቅላላው በዚህ አመት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ስለ
ወሰዳቸው እርምጃዎች ያለንን አስተያየት ባጭሩ ለዚህ ጉባኤ እንድገ
ልፅ ተጠይቄአለሁ።

ሀምሌ ሰባት ቀን ሀይለ ስላሴ ወደዋሽንግተን ከተማ መም
ጣቱን ምክንያት በማድረግ የአለም - አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎችን አ
ቋም በይፋ የሚያሳውቅ ታላቅ ሰልፍ ለማድረግ ወሰንን። በመጀመሪያ
ይህንን ሰልፍ ለማድረግ ያቀድነው በሚያርፍበት የአሮፕላን ማቢያ
ነበር፣ግን የበላይ ጠባቂው የአሜሪካን መንግስት ታላቅ ጥንቃቄ በማድ
ረግ ከከተማው ወጣ ብሎ በሚገኘው የአየር - ሀይል ማቢያ እንዲያርፍ
በማድረጉ እቅዳችንን ልንሰራበት አልቻልንም።የአየር- ሀይል ማቢያው
ሰፈር ለመድረስ ጨርሶ የማይቻል በመሆኑ የመጀመሪያውን እቅዳችን
ን መቀየር አስፈለገ።

ልክ ሀይለ ስላሴ ዋሽንግተን በደረሰበት ሰአት ከሰሜን አ
ሜሪካና ከካናዳ የተሰበሰቡት ሰማኒያ ያህል እህቶችና ወንድሞች ወደ
ኢትዮጵያ ኤምባሲ ሄዱ፤ዘበኝነት የቆመ ፈጥኖ ደራሽ ፓሊስ በመኖሩና
የኤምባሲው መግቢያዎች ሁሉ ከውስጥ በመቆለፋቸው በሀይል መግባ
ት አስፈላጊ ሆነ፤በሩንና መስኮቱን ሰባብረው ገቡ።ቤቱ ውስጥ የተገኙ
ት የህዝብ መደለያ እቃዎችና የአጉል መመፃደቂያ ፅሁፎች በሙሉ በ
አንድ አፍታ ወደሙ፤በጭር ጊዜ ውስጥ የሚሰባበር እቃ ጨርሶ ጠፋ።
ባሜሪካኖቹ ግምት የተደረገው ጥቃት አስር ሽህ ዶላር ያህል ይደርሳል።
በተሰባበሩትና በወደሙት የመመፃደቂያ ፅሁፎች ምትክ ስለኢትዮጵያ
ህዝብ ትግል የሚገልፁ ሬቮሉሽናዊ መግለጫዎች ተለጥፈው ነበር።

በኤምባሲው ውስጥ ለማድረግ ያሰብነው እንደተፈፀመ ለ
መቆየት ከተመደቡት ጓዶች በስተቀር ሌሎቹ ከፓሊስ እያመለጡ ሀይለ
ስላሴ ወደሚገኝበት ወደ"ሁዋይት ሀውስ" አመሩ። እዚያም በ"ሁዋይት
ሀውስ"ና ሀይለ ስላሴ ባረፈበት ቤት መሀል ባለው ስፍራ ላይ ትልቅ ሰል
ፍ ተደረገ።ፅሁፎችን በመበተንና ንግግሮችን በሚድረግ ሀይለ ስላሴን ለ
መቀበል ተሰብስቦ ለነበረው ህዝብና ለአላፊ አግዳሚው ስለጨቋኙ አገ
ዛዝ በደንብ አሳወቅን። ተጠባባቂዎቹ አሜሪካኖች የሰልፉን ጥንካሬ ስ
ለተረዱት በ"ሁዋይት ሀውስ" የታቀደውን እሽጉድ ማስቀረት ግድ ሆነ
ባቸው።እያለሁ ብሎ የተሰበሰበው ህዝብም ሶስት ሰአት ከተንቃቃ በኋ
ላተበታተነ፤ሀይለ ስላሴም ያረፈበት ቤት ውስጥ ተደብቆ አደረ።

ይህ በሚሆንበት ጊዜ ኤምባሲው ውስጥ የቆዩት እህቶቻች
ንና ወንድሞቻችን ትግል ይቀጥል ነበር።የዋሽንግተን ፖሊስ ኤምባሲው
ም ውስጥ ሆነ ባቅራቢያው ያሉትን ጓዶች ያለምህረት ይደበድባቸው ጀ
መር፤ብዙ ጓዶች ቆሰሉ፤ከዚያም የኤምባሲው አንደኛ ፀሀፊ በተባለ ቡች
ላ አመልካችነትና ልመና አስራ-አራት ጓዶች ተያዙ። ከብዙ ድብደባና
ስድብ በኋላ አስራ-አራቱም ጓዶች ወደ እስር ቤት ተወሰዱ። ለመያዛቸ
ውና ለመታሰራቸው የተሰጡት መሰረተ ቢስ ምክንያቶች እንደ ቤት ሰ
ብሮ መግባት፤እንደእቃ ማጥፋትና ባልተፈቀደ ስፍራ መሰብሰብ፣ እንደ
ፓሊስ መደብደብና ይህን የመሳሰሉ ነበሩ።እነዚህ ክሳች ለማጭበርበሪያ
ለመጨቆኛያና ለማስፈራሪያ የታቀዱ ሲሆኑ፣ ዋናው ምክንያት ለፍርድ

ግምደላቸው የተፈጠሩ ዘዴዎች ናቸው። ይህን ለመረዳት አንድ ምሳሌ መጥቀስ ይበቃል፣ፖሊሶች አንዱን ወንድማችንን መሬት ጥለው ሲያጠቁ ሳለ አንዲ እህታችን ስለተከላከለችለት ፓሊስ ደበደብሽ ብለው ያዧት።

በ"ሁዋይት ሀውስ" ታቅዶ የነበረው መስተንግዶ ለማግስቱ በቀጠሮ አድሮ ነበር።በዚሁ እለት እንደገና ብዙዎች ጓዶቻችን በ"ሁዋይት ሀውስ"ፊት ለፊት ሰልፍ አደረጉ፤ በሰልፉም ምክንያት ሀይለ ስላሴ ወደ ፈንጠዚያው መድረስ አልቻለም።ብዙ ሰአት ካሳለፈ በኋላ በፓሊስና በወታደር ተከቦ ደረሰ።ድግሱ ቤት በነበረበት ሰአት ሁሉ ሰልፉ ቀጥሎ ነበርና፣በሀይለ ስላሴ መሪነትና በኢምፔሪያሊስቱ አሜሪካን የበላይ ተጠባባቂነት የኢትዮጵያ ፊውዳል ስርአት በኢትዮአያ ህዝብ ላይ የሚፈፅመውን ጭቆናና ብዝበዛ የሚያብራሩ ሀተታዎች ስእሎችና ልዩ ልዩ መልእክቶች በሰፊው ታደሉ።

ይህ ጠንክራ ሰልፍ ታላቅ ስጋት ስላሳደረ ሀይለ ስላሴ ከ"ሁዋይት ሀውስ"ሊወጣ አልቻለም። ስለዚህ ፓሊሶች ከማፈሻ መኪና ጋር ወደ ሰልፉ መጥተው አስር የሚሆኑ ጓደኞቻችንን ያለምንም መግለጫ አፍሰው ወደእስር ቤት ወሰዷቸው፤ ሰልፉንም በሀይል ከለከሉ። ሆኖም ፍርሀታቸው ባለመቀረቱ፤ አሶተባበይ መኪናዎች ከነአጃቢያቸው አምስት ጊዜከ"ሁዋይትሀውስ"ከወጡ በኋላ ሀይለ ስላሴ በስድስተኛው መኪና በፓሊስና በወታደር ተከቦ በጥድፊያ ወጣ።

በነዚህ ጥቂት ቀናት ውስጥ በሰሜን አሜሪካ የተደረገው ትግል ባለፉት አመታት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ከደረጓቸውና አሁንም በያለበት ከሚያከናውኗቸው ትግሎችና ተቃውሞዎች ተነጥሎ ሊታይ አይችልም።ከ1965 እ.ም.(እ.አ.አ.)ጀምሮ መጀመሪያ የከተማውን ድሀ ማጐሪያ የሆኑትን ወህኒ ቤቶች በመቃወም፣ከዚያ «መሬት ላራሹ» በማለት፤ቀጥሎም ሰላማዊ ሰልፍን ለመከልከል የወጣውን ደንብ በመቋቋም ያደረጓቸው ሰላማዊ ሰልፎች ቀጥተኛ ተከታይ ነው። በተለይም የዚህ አመት የብሄራዊ ተማሪዎች እንቅስቃሴና እስታሁን ሊገታ ያልቻለው ትግል፤በአለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር መሪነት በውጭ አገር የተደረገው የኤምባሲዎች ወረራና ለጥቂት ሰአቶች ነፃ



መውጣት መነሻውና መሰረቱ ሆነዋል ለማለት ይቻላል።

ትግል ትግልን ያስከትላል፣የትግልንም እውቀት እያበለፀገው ይሄዳል።የኢትዮጵያ ተማሪዎች እስካሁን የተራመዷቸው የትግል ደረጃዎች ብዙ እውቀትን እንዳበረከቱላቸው በየጊዜው ከፍ እያለ የሄደው የትግል ተግባራቸው በገሀድ ይመሰክራል።እንደዚህ እንደሰንሰለት ተያይዞ የሚመጣው ትግል መቀጠሉ እንደማይቀር ስናምን፣በየጊዜውም ደግሞ በስፋቱም ሆነ በጥልቀቱ እየጨመረ እንደሚሄድ እንጠራጠርም።

ምንም እንኳ ተማሪዎች በየጊዜው የተሰላፉባቸው የትግል መምሪያዎች የተለያዩ ቢሆኑም፤በመሰረታቸው የፈለቁት ከበሰበሰው ስርአት ነው፤ይህን ስርአት ለማስወገድ ከተተለሙት መሪ አላማዎች ተነጥለው ሊታዩ አይችሉም።እዚህ ላይ ቆም ብለን ከነዚህ መሪ አላማዎች አንዳንድ አይነተኛ የሆኑትን አላማዎች መግለፅ ይጠቅማል ብየ አምናለሁ።

<u>የመጀመሪያ አላማ፤</u>

— የሀይለ ስላሴ ባላባታዊ መንግስት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ያወረደውን የጭቆና ማእበልና የብዝበዛ ቀንበር መቃወም። «መሬት ላራሹ! ስልጣን ለህዝቡ!» የሚሉት የትግል መምሪያዎች የሚገልፁት ይህን አላማ ነው።

ከባላባታዊው መደብ ጋር በጥቅም በመተሳሰርና የባላባታዊው አገዛዝ የፀላይ ተጠባባቂ በመሆን የህዝቡን ችግር ያፀናውን ኢምፔሪያሊዝም–በተለይም የአሜሪካንን ኢምፔሪያሊዝም–መቋቋም።ይህ ላይ ከጠቀስነው ከባላባታዊ መደብ መቃወም ተነጥሎ ሊታይ አይቻልም።ዛሬ በያዝነው የአገራችን የታሪክ ምእራፍ ውስጥ የሸገተው ባላባታዊ መንግስት ያለኢምፔሪያሊዝም –በተለይም ያለአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም– ጥገናና የበላይ ተጠባበቂነት ሊቆይ እንደማይቻል ሁሉ ኢምፔሪያሊዝም– በተለይም የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም– የባላባቱን መንግስት ችክል ሳያደርግ በአገራችን ላይ የብዝበዛና የጭቆና ድንኳኑን ሊተክል አይችልም።ሁለቱም በአንድነት ተባብረው የሚሰሩ የጥቅም ሸሪኮች ስለሆኑ በአንድ ላይ ሊወጓቸው የሚገባ ነው።

በዋሽንግተኑ የተቃውሞ ሰልፋችን ጊዜ በሰፊው የተዋጋን
ው ይህንን አላማ ለመግለፅና ሁለቱን የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላቶች(ባላባ
ታዊውን አገዛዝና ኢምፔሪያሊዝምን) ለመላው ህዝብ፤በተለይም ለወደ
ፊት ተራማጁ ሀይል ለማሳወቅ ነበር።ስለሀይለ ስላሴ በውጭ አገር የሚነ
ዛውን የማታለያ ፕሮፓጋንዳ ለማፍረስና ፀረ-ኢምፔሪያሊዝም የሆነው
ንአቋማችንን ለመግለፅ በፅኑ ተሞከረ።

በዚህ በኩል የተደረገው ጥረት ከታሰበው በላይ ፍሬ አሳይ
ቷል።ኤምባሲው ነፃ በወጣበት ጊዜና ከዚያም በኋላ ፀተደረገው ሰልፍ
ብዙ ጋዜጠኞች ተገኝተው ነበር። የተወሰደው እርምጃ ያስገኘውን ድ
ል ለመረዳት የጊዜውን ጋዜጦችና ልዩ ልዩ ዜናዎች ማየት ይበቃል።
ሀይለ ስላሴ እዚያ በነበረበት ጊዜ ሁሉ እዚያ ለመኖሩ ከተገፈው አንድ
ሁለት አረፍተ ነገር ሌላ የቀረው ዜና ስለኛ ትግል ብቻ ነበር።የሰጠናቸ
ው መግለጫዎችና ሀተታዎቻ የአብዛኞቹን ጋዜጦች የመጀመሪያ ገፅ ይ
ዘው ነበር።ስለኢትዮጵያ ህዝብ ንቅናቄ የነበረው ዜና በዚህ አለተወሰነ
ም፤ዋናው የተቃውሞ ሰልፍ ከተደረገ በኋላ በጋዜጣ በሬዲዮ፤ በቴሌቪ
ዥን ጊዜ እየተሰጠን ሰፋፊ መግለጫዎችን ለመስጠት ችለናል።በጠቅ
ላላው በሰሜን አሜሬካና በኢንተርናሽናል የዜና ድርጅቶች ስለኢትዮ
ጵያ ይህን ያህል ዜና(ምናልባት በ1960 ወታደር ከተነሳበት ጊዜ በስተ
ቀር) ተሰምቶ አያውቅም። ስለኢትዮጵያ ባላባታዊ አገዛዝ፤ስለኢምፔሪ
ያሊዝም ወደሀገራችን መግባት፤ከዚያም በላይ ስለሰፊው ህዝብና ስለተ
ማሪው ትግል ዜናዎች በሰፊው ተሰራጭተዋል። ይህ የማሳወቅ ጦርነት
አሁንም እንደቀጠለ ነው፤ከዚህም የተነሳ በሰሜን አሜሪካ ከሚገኙ የ
ወደፊት ተራማጅ ሀይሎችና በተለይም ከጥቁር አሜሪካዊ እህቶቻችን
ና ወንድሞቻችን ያገኘነው እርዳተ እጅግ ከፍ ያለ ነው።

ሁለተኛ አላማ

— ከባላባታዊው አገዛዝና ከኢምፔሪያሊዝም ጥቃት ነፃ ለመ
ውጣት የሚያስችለው መሳሪያ ምን እንደሆነ ማስረዳት። በሰልፉ
ወቅት ኢትዮጵያ ሙሉ ነፃነቷን ልትጐናፀፍ የምትችለው በህዝብ
ትግል ብቻ መሆኑን አሳውቀናል።

በአገር ቤት የሚካሄደውን ጠቅላላ እንቅስቃሴ በመደገፍ በ



ዋሽንግተን የተደረገው የተጋድሎ ዜና ለኢትዮጵያ ህዝብ መድረሱ የ
ኢትዮጵያ ህዝብ የነፃነት ትግል እንዲፋፋም በመጠኑ ይረዳዋል ብለን
ተስፋ እናደርጋለን።በዚህ በኩል በተለይ ሊረዳን የቻለው « Voice of
America»(የአሜከሪ ድምፅ)የተባለው የኢምፔሪያሊዝም የራዲዮ ጣ
ቢያ ነው።ይቅርታ ለመጠየቅና ኤምባሲውን ለማደስ አስር-ሽህ ዶላር የ
ሚከፍል መሆኑን ለማሳወቅ ሲል ለሶስት ቀኖች ያህል በልዩ ልዩ ቋን
ቋዎች ሲሰድ የነበረው ዜና ስለኛ ትግል በሰፊው እንዲታወቅ ረድቷል

ሶስተኛ አላማ

— የሚወሰዱት የትግል እርምጃዎች ሁሉ ወደሬቮሉሽናዊ ግ
ብ እንዲመሩ ማድረግ።ማንኛውም መሰረታዊ የሆነ የትግል እር
ምጃ ሬቮሉሽናዊ አላማውን ደጋፊ የሆኑትን ሀይሎች ከማመልከ
ቱም በላይ፤የነዚህ ሀይሎች መደርጃ ወቅት እንዲፋጠን መጣጣር
አለበት።ወገንንና ጠላትን መለየት፤ጠላት የሚደክምበትን ትግል
ማፋፋም፤ወገን የሚጠነክርበትንና የሚፋፋበትን እርምጃዎች መ
ውሰድና ያለማቋረጥ መታገል የማንኛውም ሬቮሉሽናዊ አለታዊ
ቀዳሚዊ ተግባር ነው።

በዋሽንግተን የተደረገው ትግል በዚህ በኩል መልካም ው
ጤት አስገኝቷል።ትግሉ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ እስከሁን በየቦታው
የኢትዮጵያ ተማሪዎች መላ ጊዜያቸውን ለትግሉ መድበዋል። በዚህም
ምክንያት ሬቮሉሽናዊው ፕሮፓጋንዳ እጅግ እያየለ ሄዷል፤ በእርዳታ
መልክ የምናገኘው የገንዘብና የእቃዎች መዋጮ ሳያባራ እንደቀጠለነ
ው።ከዚህ በፊት የሀገርን ፍቅር በይፋ ያልገለፁ እህቶቻችንና ወንድሞ
ቻችን ባሁኑ የትግል ወቅት ከታጋዮቹ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ጋር አብ
ረው የሚሰለፉና ቆርጠው የተነሱ መሆናቸውን በገሀድ አሳይተዋል።የ
ወደፊት ተራማጁ ሀይል በቁጥር ማደግ፤በፓለቲካ አስተሳሰብ መብሰል
ና በርእዮተ-አለም አስተያየቱ መጠንከር ከተገኘው ፍሬ ሁሉ የመጀ
መሪያውን ቦታ ሊሰጠው ይገባል።

እነዚህ የአለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች አላማዎች አ
ሁን በአሜሪካ፤እንዲሁም በኢትዮጵያና በአውሮፖ የተደረጉትን ሀይለ
ኛ እንቅስቃሴዎች ብቻ አይደለም የመሩት፤ የአለም አቀፍ የኢትዮጵያ

ተማሪዎች ማህበር በየጊዜው የሚፈፅመው ተግባር ሁሉ በነዚህ አላማ ዎች የተመራ ነው።እነዚህን የተፋፋሙ ተጋድሎዎች ልዩ የሚያደርጋ ቸው የኢትዮጵያ ህዝብ ትእግስት ማለቁን፤ መራራ ቁጣውንና ለትግል ቆርጦ መነሳቱን በትክክልልና በሰፊው ለማስረዳት መቻላቸው ነው ።

በሰሜን አሜሪካ እንደዚህ አይነቱን የቆራጥነት ትግል ለመ ፈፀም ያስቻለን በዚህ አመት ኢትዮጵያ ውስጥ እጅግ በሚያስደንቅ አ ኳህን የተደረገውና የሚደረገው የትማሪዎች ትግል ነው፤በኢትዮጵያ የሚ ከናወነው ትግል የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ምን ያህል እንደተራመደ ሊያስረዳ ይችላል፤ከዚህ በፊት የተማሪዎች ትግል በጠቅላላው የሚወሰነ ውና ከስራ ላይ የሚውለው አዲስ አበባ በሚገኙት በዩኒቨርስቲ ተማሪ ዎች ነበር፤በዚህ አመት መላው የብሄራዊ ተማሪ በትግሉ ተሳትፈዋል። የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ከመጀመሪያው ጀምሮ ብርቱ ተ ባባሪ ትግል አድርገዋል። ብዙ ጊዜ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ብቻቸ ውን የኢምፔሪያሊዝምን መስሪያ ቤቶች አጥቅተዋል።

ከዚህም በላይ የዘንድሮው የተማሪ ትግል የሚደነቅበት አ ንድ ሌላ መሰረታዊ ነገር አለ፤ይኸውም ትግሉ ለመጀመሪያ ጊዜ ከገጠ ር ጀምሮ ወደ ከተማ መሸገሩና በኋላም ብሄራዊ በሆነ መልክ በኢትዮ ጵያ በመላ መስፋፋቱ ነው። እንደዚህ የጋለና ሰፊ የተማሪ ትግል በኢ ትዮጵያ ምድር ሆኖም አያውቅ።ይህ ትግል በውጭ አገር ያለውን ትግ ል ሊያነሳሳውና ሊያሳድገው ችሏል።በውጭ አገር ያሉት ሁለቱ ቅርን ጫፍ ማህበራት ግኑኙነታቸውን እንዲያጠነክሩ ረድቷል።

ሬቮሉሽናዊ ድርጅት ድካሙም ሆነ ብርታቱ የሚመዘነው በተግባሩ ነው።አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር በዚህ አመ ት የወሰዳቸው አያሌ እርምጃዎች ለድርጅታችን ጥንካሬ ምስክር ይሆ ናሉ።የተሰለፈው ተማሪ ብዛት፤የፕሮፖጋንዳው ስፋት፤በመንግስቱ ላይ የተደረጉት ጥቃቶች፤የትግሉ ቆራጥነት... በጠቅላላው ሲታይ የፓለቲ ካ ነፃነት ጨርሶ በሌለበት አገር ውስጥ በተማሪ ድርጅት ሀይል ሊፈፀ ም የሚቻለው ተደርጓል ለማለት ይቻላል።ቀጥሎ በጥብቅ ሊታሰብበት የሚገባው የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንደተከማቹበትና እንደተሰለፉበት ያለ ሬቮሉሽናዊ ድርጅት በቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ (በሰራተኛውና በ



ገበሬው) መሀከል የሚፈጠርና የሚደረጅበት ዘዴ ነው። ይህን እንድና ደርግ የጊዜው የኢትዮጵያ ሁኔታና ትግሉ የደረሰበት ደረጃ ያስገድዱና ል።በህዝቡ መሀከል የሚፈጠረውና የሚደረጀው ሬቮሉሽናዊ ድርጅት ብቻ ነው ወደ መጨረሻው ድል ሊመራ የሚችለው።

በተማሪ በኩል የተደረገው ትግል የተማሪ ድርጅት ሀይል ሊያደርገው የሚችለውን ፈፅምዋል የሚለው አስተያየት በትክክል መ ገለፅ አለበት።የተማሪው ሀይል ተፈላጊውን ፈፅምዋል ማለት በዚህ መ ስመር ያለው ትግል ይገታ ማለት አይደለም። እንደዚህ አይነቱ እርም ጃ ይወሰድ እንኳን ቢባል አይቻልም።ይህ ንግግር የተሰነዘረው ስለትግ ል በምናስብበት ጊዜ ጠቅላላ አስተያየታችን በተማሪ ድርጅት ላይ ብ ቻ መወሰን እንደማይገባውና የትግሉ ዋና ምሰሶ መፈጠር የሚገባው የሰፊው ህዝብ ሬቮሉሽናዊ ድርጅት መሆኑን ለማስገንዘብ ያህል ብቻ ነው ።

በዚህ አመት በኢትዮጵያ የታሰሩትንና ከስራ የታገዱትን ለ መተካት እንኳ አሁን በደረሰበት ደረጃ መቀጠል አለበት።መንግስቱ በ ወጣው ፋሽስታዊ ህግ መሰረት የሚታሰሩት፤የሚቀጡትና የሚታገዱ ት ተማሪዎች ቁጥር እየበረከተ መሄዱ አያጠራጥርም።ይህንንና ሌላው ን የማጥቃት ዘዴ ለመዋጋትና አዳዲስ የወደፊት ተራማጅ ሀይሎችንና ቆራጥ ጓዶችን ለማፍራት የተማሪው ትግል እያደገ መሄድ አለበት።

በውጭ አገርም ያለው ችግር –ምንም እንኳ ኢትዮጵያ ውስጥ ካለው ጋር የማይመዛዘን ቢሆንም ቀሉ– ይህን ያህል ጥቂት አይደለም። ከትግሉ ጊዜ ጀምሮ የአሜሪካን መንግስት ከአድሀሪው የ ኢትዮጵያ መንግስት ጋር አብሮ በመዶለት በጓዶቻችን ላይ ልዩ ልዩ የ አመፅና የጭቆና ተግባር ፈፅምዋል።በቅርቡ በሰሜን አሜሪካ በተደረገ ው ትግል ምክንያት አንዳንዶቹን ጓዶች እየነጠለ መክሰስ ጀምሯል። ለ ምሳሌ የመጨረሻው ሰልፍ በተደረገበት ምሽት አንዱ ጓዳችን ከሌሎች ሁለት ጓዶቹ ጋር ሆኖ ጋዜጣ ለመግዛት በመኪና ወጣ ብሎ ነበር፤እንዳጋ ጣሚ የሀይለ ስላሴ መኪና በዚያ ያልፍ ስለነበር ፖሊስ ነጥሎ አቆመው፤ በፖሊስ መኪኖች ከተከበበ በኋላ እሱም መኪናውም ፀደንብ ተፈተሹ፤ ግን ምንም ነገር ስላልተገኘበት ተለቀቀ።

በማግስቱ ሁለት የ FBI (የምስጢር ፖሊስ) ባልደረቦች ያረፍንበት ሆ
ቴል ድረስ መጥተው ህይለ ስላሴን ለመግደል ቃጥተሀል ሲሉ ያዙት።
ፍርድ ቤት እስኪቀርብም ድረስ ለመፈታት ሃያ አምስት ሽህ ዶላር መ
ክፈል እንዳለበት ተነገረው።በነገታው ይህ መሰረተ ቢስ ክስ ቀረና ሌላ
ክስ ተፈጠረ፤ «ፓስፖርትህና ቪዛህ ትክክል ስላልሆነ አሁኑኑ ወደኢት
ዮጵያ ትላከለህ» ተባለ።ከዚያ ወዲህ እንደዚህ አይነቱ ጥቃት እየበዛ ሄ
ዷል።በተለይ ጓዶችን ለኢትዮጵያ መንግስት አሳልፎ ለመስጠት የሚ
ደረገው ሙከራ ከፍ ያለ ነው። የታሰሩትም ጓዶች እያንዳንዳቸው ሁ
ለት ሽህ ዶላር ካልከፈሉ አይፈቱም ተብሏል፤ በመጨረሻም ከተፈረደ
ባቸው በተከሰሱበት አንቀፅ መሰረት አምስት አመት ያህል ይታሰራሉ
ከዚህም በላይ ፍርድ ቤት ቀርቦ የተፈረደበት የውጭ አገር ሰው ወዲ
ያውኑ ወደአገሩ መላክ አለበት የሚል ህግ ስላለ፤ይህንኑ ህግ ሊጠቀሙ
በት እንደሚሞክሩ አይጠረጠርም። በዚሁ መሰረት አንድ ከካናዳ የመ
ጣ ኢትዮጵያዊ እንዲወጣ ተደርጓል።

አራት ሌሎች ጓዶች ጉዳያቸው ገና በፍርድ ቤት ክርክር ላ
ይ ነው።ለጊዜው በታላቅ ጥረት የተዋጣውን ገንዘብ በማስያዝና በሰዎ
ች ዋስትና ከእስር ቤት ሊወጡ ችለዋል፤ ከዚህም በላይ በፖለቲካ አስ
ተሳሰባቸው ወደፊት ተራማጅ የሆኑ ጠበቆች በተወሰነ ገንዘብ ለማግኘ
ት ችለናል።ዋናው አላማችንና ጥረታችን ፍርድ ቤት የሚቀርቡት ሁሉ
የተሰነዘረባቸው የሀሰት ክስ ቀርቶ ፖለቲካዊ በሆነ መስመር እንዲከራ
ከሩ ነው፤ይህ ከሆነ የፍርድ ቤቱ ክስ የኢትዮጵያን ህዝብ ችግር፤ መሰረ
ታዊ አቋሙንና የትግሉን ሁኔታ ለአለም ህዝብ በበለጠ ለማሳወቅ እን
ደሚረዳ አይጠረጠርም።የኢትዮጵያን ህዝብ ሁኔታና የጨቋኙን መንግ
ስት አድሀሪ ባህርይ ለአለም ህዝብ የማሳወቅ አላማችን ከተፈፀመ የሚ
ደረግብንን ጊዜያዊ ግፍ ሁሉ ያላንዳች ቅሬታ እንቀበላለን።

ሆኖም ይህንን ትግል ለመቀጠል፤ከትምህርት ቤትና ከስራ
የተወገዱትንና ወደኢትዮጵያ ለእስር የሚላኩትን ለመርዳት ሀይላችን
ንማደርጀትና ማጠንከር አለብን።ለሚቀጥሉት አመታት ትግሉ አሁን ካ
ለበት ደረጃ የላቀ መሆን አለበት።በኢትዮጵያም ሆነ በውጭ አገር ያለ
ው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ እየሰፋና እየጠነከረ መሄድ ያስፈል



ገዋል። አሁን በንቅናቄው ውስጥ የሚሳተፉት አባሎች አስተያየት እየ
በረታና እየበሰለ ሲሄድ ሌሎች ደግሞ ወደ ትግሉ እንዲገቡ መጣር አ
ለብን።ከዚህም በላይ በያለበት የሚገኙት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበ
ራት ፕሮግራምና ተግባር እየተቀናበረና የተግባር አከፋፈላቸውም ዘዴ
በበለጠ መልክ እየያዘ መሄድ አለበት።እነዚህን አይነተኛ ተግባሮች ከ
ስራ ላይ ለማዋል የአለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር አስፈ
ላጊውን እርምጃ ሁሉ እንደሚወስድ ባለሙሉ ተስፋ ነን።

የተማሪው ሀይል ተገቢውን ደረጃ አግኝቷል የሚለው ጠ
ቅላላ አስተያየት የተሰነዘረው በተማሪ በኩል ያለው ንቅናቄ እዚህ ላይ
ይገታ ለማለት ሳይሆን የተማሪ ንቅናቄ ባሁኑ አያያዝ እንዲቀጥልና እየ
ደረጀ እንዲሄድ፤ ከፍ ብለን እንዳመለከትነው፤ ትግሉ ወደሌሎች ብሄራ
ዊ ክፍሎች መስራጨት እንዳለበት፤በተለይም የሰራተኛ፤የአርሶ-አደርና
የተማሪ ትግል በደንብ መቀናበር እንደሚገባው በበለጠ እንድናስብበ
ት ለማስገንዘብ የሀል ነው።

በተማሪና በሌላው ብሄራዊ ትግል መሀከል ጥብቅ ግንኙነት
እንዳለ እስከሁን የኢትዮጵያ ተማሪዎች የተሰለፉባቸው የትግል መም
ሪያዎች በቂ ማስረጃዎች ናቸው።የኢትዮ ጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ከተጀ
መረበት(ሬቮሉሽናዊ ከሆነበት)ወቅት አንስቶ የቆመበት ዋና አላማ የተ
ማሪን ልዩ ችግር ለማስወገድ አይደለም።ጭቆና ካልተለየው የኢትዮጵ
ያ ህዝብ ሁኔታ ጋር ሲተያይ የተማሪ ኑሮ በጣም የተሻለ መሆኑን በመ
ገንዘብ መላ አላማችን የተመሰረተው የጠቅላላውን ህዝብ ችግር መነ
ሻ በማድረግ ነው።

ካልፈ የከተማውን ደሀ ለማፈን የተሰራውን ወሀኒ ቤት በ
መቃወም የተደረገው ሰልፍ፤ህዝቡ ከባላባታዊ አገዛዝ ስር በፍጥነት ነ
ፃ መውጣት እንደሚያስፈልገው አስረድቷል፤ከዚያም ወዲህ ሰላማዊ ስ
ብሰባን የሚያግደውን ህግ በመቋቋም የተደረገው ሰልፍ በየጊዜው ህዝ
ቡ ላይ የሚጣለውን የጭቆና ቀንበር በገሀድ ገልፆ ለማሳየት ረድቷል።
በዚህ አመት በተደረገው ትግል የትምህርትን ሁኔታ ብቻ የሚያመለክ
ቱ መስለው የሚታዩት አቋሞች እንኳን አላማቸው ሬቮሉሽናዊ፤ምንጫ
ቸው ህዝባዊ ሆኖ ይገኛል።ለምሳሌ ለትምህርትና ለፈተና የሚጠየቀው

የገንዘብ ክፍያ የድሀውን አራሹና ሰራተኛ ልጅ እንዳይማር የሚከለክለ
ው መሆኑ ተገልፅዋል። ይህ ህዝባዊ አመራር የሬቮሉሽናዊ ትግላችን
ታሪክ ከተቆረቆረበት ጊዜ ጀምሮ ያልተለየን ቢሆንም፤ባለፉት ጥቂት አ
መታት ውስጥ እየጠነከረና እየሰፋ ሄዷል። ለምሳሌ ያህል በዚህ አመት
የተወሰዱትን አንዳንድ እርምጃዎች እንመልከት።

በዚህ አመት በኢትዮጵያ የተደረገው ትግልና የፕሮፓጋን
ዳው አመራር እጅግ የሚደነቅ ነው።የተማሪ ንቅናቄ መግለጫዎች የተ
ፃፉት በቀጥታ ለአራሹ፤ለሰራተኛው፤ለተራው ወታደር፤ ለተራው ቄስ ለ
ከተማው ተጨቋኝ ነው። መግለጫዎቹ ለተጨቆነው ህዝብ ብቻ ከመቅ
ረባቸው በላይ፤እያንዳንዱን ብሄራዊ ክፍል ተስማሚ በሆነ አኳሃን በማ
ወያየት በበለጠ እንዲተባበር አድርጎታል። ለምሳሌ መንግስቱ እንደተ
ለመደው የሚደልል መስሎት ተማሪዎችን ለማነጋገር ከልክ በላይ ጥሮ
ነበር፤ተማሪዎቹ ግን እንዲህ ያለው ንግግር ዋጋ የሌለው መሆኑን በመ
ጥቀስ አልተቀበሉትም።በመጨረሻ ከገር ሽማግሌዎች ጋር ተገናኝተው
ለመወያየት ተስማሙ፤በዚህ ታላቅ ስብሰባ ላይ ተማሪዎቹ ያገር ሽማግሌ
ዎቹን ሀሳባቸውን እንዲገልፁ በትህትና ጠየቋቸው። በውይይቱ መጨ
ረሻ ያገር ሽማግሌዎቹ የተማሪዎቹን ትህትና፤ቅንነትና የሀገር ፍቅር በማ
መስገን የመንግስቱ ወሬ ሀሰት መሆኑን መገንዘባቸውን ገልፀው፤ ለተ
ማሪዎቹ ሶስት ጥያቄዎች አቀረቡላቸው፤ (1) በባእድ ሀይሎች ትመራ
ላችሁ የሚባለው የመንግስት አስተያየት እርግጥ ነው? (2) ችግራችሁ
ምንድነው? (3) ለችግራችሁስ ምን እናድርግላችሁ? የተማሪዎቹ መ
ልስ እንደዚህ ነበር።

ለመጀመሪያው ጥያቄ ይህ ወሬ አገር አፍቃሪ የሆነውን ተ
ማሪ ከህዝቡ ለመለያየት የተፈጠረ ተንኮል ነው።ለሁለተኛው እምንፈ
ልገው በፅሁፍ በቀረበው አስራ-አምስት አንቀፆች ተጠቅሷል፤ከዚህ በ
በለጠ ከህዝቡ የተለየ ምንም ችግር የለብንም ሲሉ መልሰዋል።ምን እ
ናድርግላችሁ ለሚለው ጥያቄ ይህንኑ አቋማቸውን ለመንግስቱ ሳይሆን
ለህዝብ እንዲያስተላልፉላቸው ጠይቀዋል። ይህ ስብሰባ የሚያሳየው በ
ኢትዮጵያ የሚካሄደው የተማሪ ትግል «ከህዝቡ ተማር፤መልሰህም አ
ስተምር፤ከህዝቡ ጋር በመሰለፍ አብረኸው ታገል» የሚለውን አይነተኛ



አስተያየት በተግባር ላይ እንዳዋለው ነው።

ይህ ህዝባዊ የተማሪ ትግል አሁኑኑ ፍሬ አሳይቷል።በዚህ አ
መት ከተማሪ ጋር የተሰለፈው ህዝብ ቁጥር ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ነ
ው።በጨቋኙና በተጨቋኙ መካከል ያለው ትግል እየሰፋ የሄደው በዚ
ሁ ወቅት ነው። በውጭ አገርም የሚገኙት የተማሪዎች ማህበራት የተ
ማሪን ትግል ወደ ዋናው ብሄራዊ ትግል ለማሰራጨት በበለጠ ጥረዋል
በአውሮፓ የሚገኘው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ንቅናቄ ጥናቱን
ና ፕሮፓጋንዳውን የሚያመራው ኢትዮጵያ ን ከባላባታዊው አገዛዝ ነ
ፃ ለማውጣት የሚችሉት ሀይሎች የትኞቹ ናቸው ስለሚለው ጥያቄ ነ
ው። በሰሜን አሜሪካ ያለውም የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ንቅናቄ
ይህንኑ መስመር እያፀደቀው ሄዷል። ለምሳሌ በቅርብ በሚደረገው ጠ
ቅላላ ጉባኤ ለጥናት የሚቀርበው አርእስት ‹ስለ ጉሳና የሀይማኖት ቅ
ራኔ› ነው።ስለኢትዮጵያ ህብረተሰብ መሰረታዊ ለውጥ ውይይት በተደ
ረገ ቁጥር ወደኋላ ተመልካች የሆኑ ሁሉ የመከፋፈልንና የመነጣጠል
ን አደጋ ዘወትር ይጠቅሳሉ። ስለዚህ ትግላችን ወደህዝብ በሚያመራበ
ት ወቅት ለዚህ ጥያቄ መሰረታዊ መልስ ማግኘት ከመጀመሪያዎቹ ተግ
ባሮቻችን አንደኛው ነው።

እነዚህ ከብዙዎቹ ጥቂቶቹን ለማንሳት ያህል የተጠቀሱት
ምሳሌዎች የሚያሳዩት «የኢትዮጵያ ተማሪዎች ትግል ወደ ህዝቡ ያም
ራ» የሚለው አስተያየት በተግባር ላይ መዋል መጀመሩን ነው።የተማ
ሪ ትግል በጋለ ቁጥር ከህዝባዊ ትግል ጋር ያለው ግኑኝነት እየዳበረ ይ
ሄዳል።እንግዲህ ይህ እርምጃ እየተፋጠነ እንዲቀጥል ምን ዘዴ ይበጃል

ለዚህ መልሱ አንድ ብቻ ነው።ለአሁኑ ታሪካዊ ወቅት ብሄ
ራዊ ነፃ አውጭ ድርጅት ማቋቋም ያስፈልጋል። ዛሬ በያለበት የሚካሄ
ሄደው የገበሬና የሰራተኛው፤የተማሪና የምሁራን ተጋድሎ፤የገጠርና የከ
ተማ ትግል በደንብ ተቀናብሮ በሚገባ መመራትና አስፈላጊውን አቅጣ
ጫ መሰጠት አለበት።የዚህ ጠቅላላ ትግል ሀይል የሚደረጀውና ወደ መ
ጨረሻው ግብ ሊያመራ የሚችለው በዚህን ጊዜ ብቻ ነው። ይህ ቀዳማዊ
ተግባር (ትግሉን ማቀናበርና መምራት) ከህዝቡ ፈልቆ መውጣት ባለበ
ት ነፃ አውጭ ድርጅት ትከሻ ላይ መውደቅ አለበት።ይህን ጊዜያዊና መ

ስረታዊ ተግባር በፍጥነት ከስራ ላይ ለማዋል ቆርጠን እንነሳ።

ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ይውደቁ!
አድህሬ ሀይሎች ሁሉ ይውደሙ!
የታጠቀው ህዝብ ያሸንፋል!

---

## ትግሉ በየቦታው በልዩ ልዩ ዘዴ ይቀጥላል!

## ‹የማጋለጫ ትግል›

በኢትዮጵያችን ጭብጥ የማይሞሉ ሰዎች ሙሉ ስልጣንን በጃቸው ጨብጠው በአብዛኛው ህዝብ ትከሻ ላይ አሰቃቂ የሆነ የጭቆና ቀንበር ጥለውበታል። እነዚህ ጭብጥ የማይሞሉ ሰዎች አብዛኛውን ሀብት በጃቸው በማስገባት የመላውን ሰርቶ-አደር ህዝብ የጉልበት-ፍሬ እንደ መዝገር ይመጣሉ።መፋፋት፤መልካም ጤና፤እውቀት፤መንደላቀቅ... ወዘተ. የነዚህ አልቀቶች ልዩ መብቶች ሲሆኑ፤አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ በድህነት ታስሮ፤በበሽታ ተቆራፍዶ፤በመሀይምነት ተጋርዶ፤ሰብአዊ መብቱን ተገፎ ይገኛል ።

ይህ ሁሉ ሲሆን የዚህ ሁሉ አላፊ የሆነው ፊውዳሉ የኢትዮጵያ መንግስት ከነአድህሬ መሬው በየውጭ አገሩ (በተለይ በአውሮፓና በአሜሪካ)የገነነ ሰምና ዝና አለው።ይህ መቼም የሚያስገርም አይደለም፤የጥቅም ግብር-አበሮቹና የበላይ ተጠባባቂዎቹ ከሚያደርጉለት የሀሰት ፕሮፓጋንዳ የተነሳ ነው።ይህ የሀሰት ፕሮፓጋንዳ መሰበር አለበት፤ እነዚህን የሀሰት ፕሮፓጋንዳ ጉንጓኞች ማስተባበል ያስፈልጋል። ለሰፊው ህዝብና ለወደፊት ተራማጅ ሀይሎች የኢትዮጵያን እውነተኛ ሁኔታ ማስታወቅ ይገባናል።

በውጭ አገር የሚገኙ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት እንደዋና አላማ አድርገው ከወጠኗቸው ተግባሮች መካከል አንዱ ይህ የ



ሀሰት ፕሮፓጋንዳ ማስተባበልና የኢትድጵያን እውነተኛ ሁኔታና የአድሀሬውን መንግስት ፋሽስታዊ አቋም ለአለም ህዝብ የማሳወቅን ተግባር ነው።ይህንንም አላማ ከግብ ለማድረስ በልዩ ልዩ ዘዴዎች (ኤምባሲዎችን መያዝ፡ዕህፉችን ማውጣት መግለጫዎችን መስጠት...) ይጠቀማሉ።

ባለፈው ጊዜ በየቦታው የኤምባሲዎች መያዝ፡በአንዳንድ ቦታዎች የተደረጉት ሰላማዊ ሰልፎች፤በብዙ ስፍራዎች ለጋዜጦች፡ ለራዲዮኖችና ለቴሌቪጋርኖች የተሰጡት መግለጫዎች፤ከወደፊት ተራማጅ ሀይሎች ጋር የተዘረጉት ግኑኝነቶች... ለዚህ «የማጋለጥ ትግል» እንደረዱን የታመነ ነው። በተመቸ ቦታና ጊዜ ሁሉ እነዚህን የመሳሰሉትን ድርጊቶች በበለጠ መቀጠል አለብን።

ከኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በግፍ እየተዘረፈ በተበተነው ገንዘብ እንደባቢሎን ጣብ የተከመረው ስምና ዝና እንደፍግ ክብ እየተፍረከረከ መውደቅ ጀምሯል።አድህሬው መንግስት ካሁን ወዲያ በሽሽግ ወጥቶ በሽሽግ ይገባ እንደሁ እንጂ፤እንደለመደው በየቦታው እየዞረ መደንፋት አይችልም። ድሮውንስ ያልሰሩትን «ሰራሁ» ያላፈሩትን «አፈራሁ» ያልሆኑትን «ሆንሁ» እያሉ መውሻከት ከየት ሊያደርስ ኖሯል?

ለኛ አንድ መሰረታዊ ነገር ግልፅ ነው፤አድህሬው መንግስት ከስረ መሰረቱ እስታልተነቀለ ድረስ፤የበላይ ተጠባባቂው ኢምፔሪያሊዝም –በተለይም የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም– ከሀገራችን እስታልጠፋ ድረስ፤ በነዚህ በሁለቱ የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላቶች መቃብር ላይ የላብ አደሩን ህዝብ መብትና ጥቅም ያለማቋረጥ የሚያንከባክብ ህዝባዊ መንግስት እስታልቆመ ድረስ ከያዝነው ትግል አንዲት ቅንጣት እንኳን አናፈገፍግም።

በዚህ አመት በሉንድ ከተማ ለተደረገው ዘጠነኛ ጠቅላላ ጉባኤ ከታቀዱት የስራ ፕሮግራሞች አንዱ ይህን «የማጋለጥ ትግል» ከተግባር ላይ ለማዋል ነበር።ለዚህም ግብ ከተወሰዱት እርምጃዎች አንደኛው የኢትዮጵያን ሁኔታ የሚያሳዩ ስእሎችና ፎተግራፎች በኤግዚብሽን መልክ አዘጋጅቶ ማቅረብ ሲሆን፤ሁለተኛው ደግሞ ከአንድ ከተማ ወደ ሌላ ከተማ የተደረገው የሃያ ኪሎ ሜትር የእግር ጉዞ ነው።

## የዘጠነኛው ጠቅላላ ጉባኤ ኤግዚቢሽን

ኤግዚቢሽኑ በመጠኑ የተወሰነ ቢሆንም ቅሉ ያው ያለው በ መልካም ሁኔታ ተቀናብሮ በመቅረብና ቅደም ተከተሉ የተሳካ በመሆኑ ለብዙዎቹ ተመልካቾች የተምዋላ አስተያየት ሊሰጥ ችሏል። ተመልካቹ ኤግዚቢሽኑ ወደሚታይበት አዳራሽ ሲገባ በመጀመሪያ የሀገሪቱን ፍጥረታዊ ሀብት የሚያሳዩ ስእላዊና ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ይመለከታል።ከዚህ ቀጥሎ፡«ሀገራችን እንደዚህ ሀብታም ናት፤ግን ህዝቡ የሚገኝበት የድህነት ሁኔታ ይህ ነው፤» በማለት ስለህዝቡ ድህነት የሚያመለክቱ ስእሎችና ስታቲስቲኮች ተደርድረው ያያል።እነዚህም በክፍል በ ክፍል ተለይተው ስለጤና፤ስለትምህርት፤ስለኑሮ፤ስለልማት ዝቅተኛነት... ያሳዩ ነበር። ከመሀል ጐልቶ ይታይ የነበረው ህዝቡ በእንደዚህ አይነት አሰቃቂ ሁኔታ ሲገኝ ሳለ አድሀሪው መንግስት እነዚህን ሁኔታዎች ለ ማሻሻል ጨርሶ የማያስብ መሆኑን ለማስመስከር ቀርቦ የነበረው የበጀት ግራፍ ነበር።በዚህ ግራፍ ላይ የሚታየው ለህዝቡ አስፈላጊ ለሆኑት ነገሮች ሁሉ የሚደለደለው በጀት እጅግ ዝቅተኛ ሆኖ ሳለ፤ለወታደርና ለፀጥታ የተመደበው በጀት በጣም ከፍተኛ መሆኑን ነው።

ከዚሁ በማያያዝ «የወታደሩና የፀጥታው በጀት በምን ምክንያት ይኸን ያህል ሊሆን ቻለ ?» ብሎ ከጠየቀ በኋላ፤«የህዝቦች ትግል» በሚል አርእስት ስር የፊውዳሉ ስርአት እንገፍግፎት ስለተነሳው የኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ያሳያል።አሁን በውጭም ሆነ በውስጥ የአድሀሪውን መንግስት በመቃወም ስለሚካሄዱት የሰራተኛ፤የገበሬና የተማሪ ተጋድሎዎች ስእላዊ መረጃዎችን ያቀርባል። በመጨረሻ የጐብኚው አይኖች «የኢትዮጵያ ህዝብ ተነስቷል ! አድሀሪው መንግስት እየተንከተከተ በመውደቅ ላይ ነው ! የኢትዮጵያ ህዝብ ያሸንፋል ! › የሚሉ ሬቮሉሽናዊ ፅሁፎች የሰፈረበት ግዙፍ ሰሌዳ ላይ ያርፋሉ።

ከኤግዚቢሽኑ አዘጋጅ ኮሚቴ እንደተረዳነው ኤግዚቢሽኑን ወደ አምስት መቶ ተመልካቾች ያህል ጐብኝተውታል።አብዛኞቹ ጐብኝዎች ‹እኛኮ እስካሁን በምንሰማው ዜና "የሰላም አገርና በእድገቷም ከፍተኛ የሆነች አገር... "ትመስለን ነበር፤ » እያሉ በመደነቅ ከትግላችን ጋር ያላቸውን አንድነት ገልፀዋል። በተለይም በኤግዚቢሽኑ ወቅ



ት በእንግሊዘኛ ቋንቋ ተዘጋጅተው ይሸጡ የነበሩት ሁለት መፅሄቶች (News from Home and Washington : The Struggle Continues; Some Facts on Ethiopia) በብዙ ይገዙና ይነበቡ ነበር።

ስብሰባው በተደረገበት ከተማ የሚታተሙት ጋዜጦችም ስለኤግዚቢሽኑ ሀተታዎች አቅርበዋል።Arbetet (ሰራተኛው) የተባለው ጋዜጣ በ12.8.69 «የኢትዮጵያ ተማሪዎች በእናት አገራቸው ውስጥ ህዝባዊ መንግስት እንዲመጣ ይታገላሉ» በሚል አርእስት ስር ባወጣው ፅሁፉ ስለስብሰባው አላማና ስለኤግዚቢሽኑ በሰፊው አትቷል።

ኤግዚቢሽኑ እጅግ አስደስቷቸው የነበሩ ቅርንጫፍ ማህበራት በያሉበት ሀገር ያሳዩ ዘንድ ማስረጃዎች እንዲላኩላቸው ጠይቀዋል። በኤግዚቢሽኑ ላይ ቀርበው ከነበሩት ስእሎችና ማስረጃዎች አንዳንዶቹ በነሀሴ ወር ይጀመር በነበረው ‹ በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር አስራ-ሰባተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ»እንዲታዩ ተልከዋል።የተገኘው ውጤት አጥጋቢ መሆኑን በመመልከት የዚህ አመት ስራ አስኪያጅ ኮሚቴ ይህ ኤግዚቢሽን በየቦታው እንዲታይ የተቻለውን ሁሉ ያደርግ ዘንድ በጥብቅ እናሳስበዋለን።

---

## የኢትዮጵያን ህዝብ ትግል ለመደገፍና ፋሽስቱን የኢትዮጵያ መንግስት ለማጋለጥ የተደረገው የሃያ ኪሎ ሜትር የግር ጉዞ

ዘጠነኛው ጠቅላላ ጉባኤ የተሰበሰበበትን ተግባር በሚያከናውንበት ወቅት ከመበታተኑ በፊት

— ተፋፍሞ ያለውን የኢትዮጵያ ህዝብ ትግል በአንደበት ብቻ ሳይሆን በተቻለው ተግባር ጭምር ደጋፊ መሆኑን ለመግለፅ

— በውጭ የሚካሄደው የተማሪዎች ትግል የአገር ቤቱ ትግል አካል መሆኑን ለማስታወቅ

— የኢትዮጵያን ህዝብ ሁኔታ ለተሰበሰብንበት ሀገር ህዝብ ለማሰማት

— ስሙ በሀሰት ፕሮፓጋንዳ የገነነውን የኢትዮጵያ መንግስት እውነተኛ ባህርይ ለህዝብ ለማሳወቅ




በ18.8.69. ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ተወስኖ ነበር። በውሳኔው መሰረት ቁጥራቸው ወደ ሰማኒያ የሚጠጋ ተማሪዎች ከተሰበሰቡበት ከተማ (ከ ሉንድ) አንስተው ሃያ ኪሎ ሜትር እርቆ እስተሚገኘው ፣ማልመ እስ ተሚባለው ከተማ ድረስ በግር በመጓዝ ሰላማዊ ሰልፍ አድርገዋል። በጉዞው ወቅት ልዩ ልዩ መዝሙሮችን ይዘምሩ ነበር። በተለይም በፈረ ንሳይ የቅርንጫፍ ማህበር ተቀናብሮ የቀረበው «መሬት ላራሹ» የሚለ ው መዝሙር ተደጋግሞ ተዘመረ። ከዚህም ሌላ «አትለውም ወይ፣አትለ ውም ወይ! የህዝብ ወታደር አይደለህም ወይ! በለው! በለው! አትለው ም ወይ አትለውም ወይ! የገበሬው ልጅ አይደለህም ወይ! በለው! በለ ው!» እያሉ ቀድሞ ይታወቁ የነበሩ ዜማዎችን በሬቮሉሽናዊ ግጥሞች እያደሱ ይዘምሩ ነበር። በሉንድ ከተማ፣ በሃያው ኪሎ ሜትር የግር ጉዞ ወቅትና በማልመ ከተማ ውስጥ የኢትዮጵያን ህዝብ ሁኔታ የሚያብራ ሩ ፅሁፎች በሰፊው ታደሉ፣ተበ ተኑ። ተጓዦችም ይዘዋቸው የነበሩት ሰ ሌዳዎች የጉዞውን ምክንያት በብሩህ የሚያሳዩ ፅሁፎች ሰፍረውባቸው ነበር። ከነዚህም አንዳንዶቹ፡ «መሬት ላራሹ! የኢትዮጵያን ህዝብ ትግል እንደግፋለን! የኢትዮጵያ ሰራተኞች፣ገበሬዎችና ተማሪዎች ተዋሀዱ! የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላቶች ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ናቸው፤ ትግላችን ፀረ-ፊውዳሊስት ፀረ-ኢምፔሪያሊስት መሆን አለበት! ህዝባ ዊ መንግስትን እንደግፋለን፤ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን እንቃ ወማለን! አለም በቃኝ ይውደም! ያሰርካቸውን ተማሪዎች ፍታ! የኢ ትዮጵያ ህዝብ ያሸንፋል! ... » የሚሉ ነበሩ።

በጉዞው መጨረሻ ተሰላፊዎቹ በአንድ አማካይ የሆነ አደ ባባይ ላይ ተሰብስበው «መሬት ላራሹ» የተባለውን መዝሙር ደጋግመ ው ከዘመሩ በኋላ ስለጉዞው አላማ፣ ስለጠቅላላው አቋማችንና ስለኢት ዮጵያ ሁኔታ የሚገልፅ ንግግር ተደርገ። ለህዝብ የታደለውን ማጋለጫ ፅሁፍና በጉዞው መጨረሻ ከአደባባዩ ላይ ተሰብስቦ ለነበረው ህዝብ የ ተደረገውን ንግግር በሚቀጥለው ገፅ ተመልከት።




18th. August, 1969 .

Dear Comarades,

Hardly noticed by any of the democratic forces in the world a fascist type dictatorship reigns in Ethiopia today. The reactionary feudal regime day by day continues to add to its already numerous criminal acts against innocent people and struggles to strengthen its ruthless grip on its police state. Its recent history is the story of " pacification " programmes and of futile efforts to convince the working population that its systematic sell-out of the country to World Imperialism is in fact a development programme.

The Ethiopian economy is a feudal economy distorted by the methodical penetration of Imperialism. Over 90% of the land is owned by powerful feudal barons and the Imperial family. They weld extensive political power unparalleled by any country in the world, the peasants are obliged to pay

by law over 75% of their produce on land. The feudal chiefs can exhort all their impositions by the application of torture and other means of coercion which is easily available from the police force, military and paramilitary units. The general health of the population - i.e. of the labouring masses - is in the worst of conditions. They are victims of all kinds of parasite diseases, tubercluosis, leprosy, venereal disease etc. Such is the general state of affairs that there is hardly any country in the world which houses a population living in such downgraded misery and periodic starvation. As a result of these there have been many heroic peasant uprisings in violent protest of the feudal system of ownership and appropriation. At present there are many peasant armed struggles in at least five provinces in the country. The provinces of Bale, Gojjam, Sidamo, and Eritrea - which are the scenes of the armed



struggle are under a brutal military administration. Many villages continue to be indiscriminately bombed, innocent people are tortured and put to jail.

The conditions of workers is terrible and miserable. The streets of all the big towns are thronged by many potentially resourceful youngsters victimized by a system which awards a tiny minority at the expense of the immeasureable majority. It is against this backgroundthat the cities and towns have in recent years and months been the scene of pitched battles between the repressive forces of the feudal regime and the innocent citizens. The workers in the factories have become vigorously articulate against their very low pay, poor health conditions and insecurities etc. Workers in some factories such as in the Ethio-Dutch Sugar Plantation in Wonji, which has 20,000 workers, has been forcefully occupied by the workers.

The educational condition of the country is

no better than the rest. 95% of the population is illiterate. The government has declared that it can afford to take to schools only 500,000 students out of a school-age children of 11 million. This means that it has places for only 5% of the school-age population. There is one university in a country of 25 million and has a total of two thousand students.

The students and intellectuals of the country thus have been for many years consistently vociferous in their total opposition of the feudal regime. The students have come to the conclusion that nothingcan be attainable without a basic structural change in the socio-economic set-up of the country. The students had demonstrated on many occassions against the unjust system of land ownership, against the proclamation on the Prohibition of Peaceful Demonstrations. They have shown their opposition to the cultural aggression by the



US peacecorps. ( The Peace Corps has its largest contingent in Ethiopia compared with any other country in the world. )

Particularly beginning from the month of February this year and for months on there has been a general student uprising supported and sympathized by the working masses. The uprising was sparked by the fascist murder of a pupil, and when the students opposed this cold-blooded murder the repression became wide spread and schools were forcefully closed, tens were brutally murdered and hundreds of them are at present undergoing torture. Some have been sentenced for five and eight years. Some are in prison on similar charges. The schools and colleges in the country have been closed from the month of February and onwards.

The opposition of the Ethiopian students abroad has been immediate and decisive. They supported the actions of their comarades at home and

fully supported their demands. They expressed this by the occupation of the feudal regime's embassies in Washington, Moscow, Paris, London, Belgrade and Stockholm in the end of March and the beginning of July. They had many demonstrations against the repression in Ethiopia in several countries of the world.

Recently the feudal regime represented by Haile-Selassie has reduced itself to a vassal state of US Imperialism. It shamelessly bargains the rights of our people, the independence of our country and conspires in a global, continental and regional counter-revolutionary manoeuvres. About two months ago, Haile-Selassie, the tyrant, went to the United States to bring more guns for the suppression of our people. Violently angry at this unique traitorous act in the history of our people, the Ethiopian Students in North America stormed the feudal regime's embassy in protest of the



oppressive regime's acts. Thereupon, a United States Police contingent mercilessly attacked the students, detained them and continues threatning them with all kinds of criminal charges.

The democratic forces in the world should come to the reality that the feudal regime in Ethiopia which is propped and armed by Imperialism faces the iron determination of the people to free themselves from feudal domination. And to that end they have taken up arms to free themselves in the absence of any genuine alternative to the bonds feudalism and semi-slavery. This has become particularly apparent after the declaration of the Detention Act of April 7th. 1969. According to this any Ethiopian is liable for any period of detention dependent upon the discretion of the Minister of Interior. This is obviously a calculated and desparate effort tostifle the opposition which has grown to formidable proportions.

We dedicate ourselves to the efforts to liberate the Ethiopian masses from a feudo-fascist dictatorship functioning under the umbrella of Imperialism.

We firmly support the struggle of our compatriots agaist the reactionary regime's oppression and acts of treason.

We strongly support the heroic struggle of our people to liberate themselves from the joint oppression of feudalism and Imperialism.

We strongly condemn the fascist law under operation in our country and reaffirm our solid determination to fight for a democratic Ethiopia.

Down with feudalism !

Down with imperialism !

Long live the struggle of the Ethiopian people !

The Ethiopian masses will triumph !



POVERTY, IGNORANCE, DISEASES and OPPRESSION CHARACHTERISE ETHIOPIA TODAY.

1. 98% of the population in Ethiopia are illiterate.
2. More than 60% of the children in Ethiopia die before the age of 5.
3. Average per capita income is US $ 35 per year.
4. Peasants do not own the land they till; the landlords' levy is up to 75% of their crop yield.
5. THE FEUDAL REGIME OF HAILE SELASSIE IS LACKEY TO US - IMPERIALISM.

THE PEOPLE OF ETHIOPIA STRUGGLE AGAINST FEUDALISM AND IMPERIALISM

Peasants are conducting armed struggles throughout the country. They are suppressed by the feudal regime with bombs and napalm with the direct support of US- Imperialism. Ethiopia will be another Vietnam.

Workers are resolutely struggling against imperialist exploitation. Ethiopian students are struggling throughout the world against the dictatorial regime of Haile-Selassie and US-Imperailism, both of which oppress the Ethiopian people.

During the biggest Student Uprising this year

- more than 20 students were killed
- more than 20 were sentenced to prison terms ranging from 6 monthes to 71/2 years.
- more than 2000 students were put in concentration camps.
- all schools and the University were closed and are still closed.
- Ethiopian students in USA and Europe occupied their embassies.

In July, during Haile Sellasie's pilgrimage to Washington Ethiopian students in North America occupied the embassy and destroyed all articles of propaganda. They forced the dictator to sneak in and

out of the White House protected by the American security police.They exposed to the American people the feudalist and imperialist oppression in Ethiopia. As a result 25 Ethiopian students have been arrested, of which 4 are still in prison.

The present popular uprising is only the beginning of the protracted struggle that will at the end free Ethiopia from both FEUDALISM and IMPERIALISM.

THE ETHIOPIAN MASSES WILL TRIUMPH








የ9ነኛው ጠቅላላ ጉባኤ ጥናት ውጤቶች ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ 'በታጠቅ'(ልዩ ቁጥር) እየተከታተሉ ይወጣሉ። እነዚህን ጥናቶች ለማግኘት የሚፈልጉ ሁሉ ከዚህ በታች በተሰጠው አድራሻ ቢጠይቁ ወዲያውኑ እንልክለን።

ማሳሰቢያ፡- ቅርንጫፍ ማህበራት ባሉበት ቦታ የሚገኙ ጓዶች በቅርንጫፍ ማህበር ስራ አስኪያጅ ኮሚቴ በኩል ይደርሳቸዋል።

Box 3198
103 64 STOCKHOLM 3
SWEDEN

## የስዊድን አገር ጋዜጦች ያቀረቡት ትችት

የሃያው ኪሎ ሜትር የግር ጉዞ በስዊድን አገር ጋዜጦች ውስጥ የመጀመሪያው ገፅ ተሰጥቶት ነበር፤የራዲዮ ጣቢያዎችም ደጋግመው አውርተውታል።አንዳንድ ጋዜጦች በሰፊው በማተት፣ በማጋለጫ ፅሁፎችን ላይ ስለሀገራችን ሁኔታና ስለህዝቡ ትግል ሰጥተነው የነበረውን ዜና ደጋግመው ፅፈውታል። በጠቅላላው ስንመለከተው የተደረገው የግር ጉዞ በስዊድን አገር ውስጥ መልካም ውጤት አስገኝቷል።ብዙ የስዊድን ዜጎች በአድሀሪው መንግስት ተጨቁኖ ስለሚገኘውና ለነፃነቱ ስለሚታገለው የኢትዮጵያ ህዝብ ሁኔታ ለማወቅ ችለዋል፤ብዙ የህዝብ ድርጅቶች፣ የተማሪ ማህበሮችና የወደፊት ተራማጅ ሀይሎች ለማወቅ ያላቸው ፍላጐት ተነሳስቷል።በያለንበት ያለማቋረጥ በመዋጋት አድሀሪውን መንግሳት ማጋለጥ ከዋና ተግባሮቻችን አንዱ መሆን አለበት። ትግላችንን እንቀጥል !

ጉባኤውን መነሻ በማድረግ፤በኤግዚቢሽኑ ውስጥ በታየውና በሰልፉ ጊዜ በተሰጠው ማስረጃ ላይ በመመስረት የስዊድን አገር ጋዜጦች ስለኢትዮጵያ ሁኔታ፣ ስለአላማችንና ስለትግላችን የፃፉትን በሙሉ ሳይሆን በከፊል ከዚህ ቀጥለን እናቀርባለን።

SKÅNSKA DAGBLADET 19/8-1969 (Extracts)

PHYSICALLY FIT ETHIOPIAN STUDENTS "PROTEST MARCHED" LUND TO MALMÖ

Nearly one hundred Ethiopian students demonstrated on Monday against the present conditions in their home country. The demonstration was unique in that they marched all the way, lund to Malmö.



Apparently there was nothing wrong with the physical fitness of the young demonstrators who marched in good style up to the statue of Charles X in the Storatorget, Malmö. They expressed by way of songs and speeches their solidarity with the struggle of the Ethiopian people, and their disgust towards the regime now ruling the country.......

The march was the culmination of the ESUE—Ethiopian Students Union in Europe — 9th. Congress that took place in Lund where some 125 delegates were present....

The purpose of the demonstration was to draw attention to the oppression which, according to the students, prevails in Ethiopia.... Songs about the Ethiopian peasants and workers who " shall win" were sang by the students, and one of them described about the oppression of the people by the regime, about starving children and about tortured people. A member of Clarté in Lund gave a declaration of solidarity with the Ethiopian students action....

A KICK AT SWEDEN

Most of the attacks were naturally directed against the oppression in their home land but Sweden too got her share with slogans such as " Down with the Swedish Imperialism" and " Swedish aid supports Haile Selassie", etc....

Seen from the organisers´ side the demonstration, which was accomplished without any intermezzo, was probably not a total success. This was primarily because the "message" was delivered in English, and without a loudspeaker as that. This drawback was, however, compensated to some extent by the leaflets distributed to the audience of some hundred persons present.

SYDSVENSKA DAGBLADET SNÄLLPOSTEN (SDS) 19/8 1969

( Extracts )

PROTEST MARCH LUND - MALMÖ

About 60 Ethiopian students from some ten differe-nt countries started on Monday a protes march from Lund to Stortorget in Malmö to express their indi-gnation against Haile Selassie's regime which was torn open by placards with slogans written in English, French and Swedish....

The demonstration against Haile Selassie's "dictatorial regime" and " US-imperialism" was in conclusion of a week-long congress in Lund organi-sed by the Ethiopian Students Union in Europe.... According to the placards more than 20 students were killed in the bigest student uprising, over 20 received prison sentences from 6 months to 7½ years, and more than 2000 were put in concentration camps....

Haile Selassie is considered as " base " of the United States in Ethiopia, where its people stru-ggle against feudalism and imperialism.... One of the 20 placards carried by one of the demonstrators in the fore-front was directed against the Swedish aid to Ethiopia.

The meeting at Stortoriget which atracted many inquisitive people was introduced by a short agi-tational speech in the Ethiopian language. During the whole march along Lundavägen-Östra Förstadsgatan-Östergatan the demonstrators sang war songs, while an advanced group distributed leaflets in Swedish where, among other things, it was stated that 98% of the people in Ethiopia can neither read nor write, more than 60% of the children die before the age of 5, and that the average income is 175 Swedish crowns per year.

DAGENS NYHETER (DN) 19/8 1969

( The biggest morning paper in Sweden )

( Extracts )

PROTEST MARCH AGAINST HAILE SELASSIE

Some 100 Ethiopian students from all over Europe belonging to the Ethiopian Students Union had assembled in Lund for a week- long congress. The congress was concluded with a demonstration march of 25 km from Lund to Malmö. The march was exacting because of the heat. The aim of the 120 participants in making this demonstration was to raise opinion for and give increased support to the struggle which their fellow students in Ethiopia are waging against the existing regime.

